AMHARIC

## ስለ COVID-19 ክትባቶች ይወቁ

# ጥያቄዎች ላሏቸው ወላጆች፡ መልሶች አሉን

አሁን የCOVID-19 ክትባት ዕድሜያቸው 5 አመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ህጻናት የቀረበ ሲሆን ይህን በተመለከተ ጥያቄዎች ሊኖሩሩት ይችላሉ። እዚህ ላይ ዩኤስ ውስጥ የሚቀርቡ የCOVID-19 ክትባቶችን በተመለከተ በአብዛኛው ለሚነሱ ጥያቄዎች ጥቂት መልሶች ቀርበዋል። ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት ዶክተርዎን ያነጋግሩ።

### Pfizer የCOVID-19-19 ክትባት ለህጻናት አስተማማኝ መሆኑን እንዴት አውቃለሁ?

የCOVID-19ክትባቶች የትኛውም አዲስ ክትባት አስተማማኝነት እና ውጤታማነቱን ለመረዳት ማለፍ የሚጠበቅበትን የመደበኛ አሰራር እያንዳንዱን ደረጃዎች አልፈዋል። ክትባቱ ለህጻናት እና አዋቂዎች አስተማማኝ እና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ በወጣቶች ላይ እና ታዳጊ ህጻናቶች ላይ በተለየ ሁኔታ ጥናቶች ተካሂደዋል። በእነዚህ ጠንካራ ጥናቶች ምክንያት፣ Pfizer የተባለው የCOVID-19 ክትባት ዕድሜያቸው 5 አመት እና ከዚያ በላይ ለሆናቸው ህጻናት እንዲሰጥ ተፈቅዷል። ለአስቸኳይ ጊዜ እንድያገለግል ፈቃድ ማግኘቱ እንዲሁም በበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከላት (CDC) በይፋ ይሁኝታ ማግኘቱን ሲታይ ክትባቱ ዕድሜያቸው 5 አመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ህጻናት ቢሰጥ ውጤታማ መሆኑን እና የመድህኒቱ በሽታ የመከላከል ጥቅም ከስጋት-አደጋዎቹ የሚበልጥ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ክትባቱን መውሰድ ህጻናትን እና ወጣቶችን ከCOVID-19 ስጋቶች እንዲጠበቁ ይረዳቸዋል።

### እነዚህ ክትባቶች በፍጥነት ሊሰሩ የቻሉት እንዴት ነው?

ከ30 ዓነታት በላይ፣ የሕክምና ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች በmRNA ክትባቶች ላይ ሌሎች ኢንፌክሽኖች እና ካንሰሮችን ለመከላከል ይረዱ እንደሆነ በማለት ጥናት ሲያደርጉባቸው ቆይተዋል። ሳይንቲስቶች በተጨማሪም ጸረ የCOVID-19 ክትባቶችን ለመፍጠር የሚያስችላቸው ምርምር ለማድረግ እንደመንደርደሪያነት ይጠቅማቸው ዘንድ፤ እንደ የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ አካል ሲንድረም (MERS) እና ድንገተኛ ከባድ የመተንፈሻ አካላት ሲንድረም (SARS) የመሳሰሉ በሽታዎችን የሚያስከትሉ ተመሳሳይ ኮሮናቫይረሶች ላይ ያዳበሩትን እውቀት እና ተሞክሮ ጭምር ተጠቅመዋል። ይህ ማለት COVID-19 በወረርሽኝ መልክነት በተከሰተበት ወቅት ዝግጁ ነበሩ ማለት ነው። በመላው ዓለም የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ የሕክምና ባለሙያዎች በተመሳሳይ ጊዜ ተመሳሳይ ችግር ላይ ሲሰሩ የነበረ መሆኑ አስተማማኝ እና ውጤታማ ክትባቶች በተሳካ ሁኔታ የመስራታቸውን ዕድል ከፍ አድርጎታል። የሰዎችን እና ማህበረሰቦችን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ይህንን ችግር ቶሎ ለመፍታት ብዙ ገንዘብ ፈሰስ ተደርጓል።

### COVID-19 በልጆች ላይ ብዙም አስቸጋሪ እንዳልሆነ ሰምቻለሁ; ልጄን ማስከተብ ያለብኝ ያለብኝ ለምንድን ነው?

COVID-19 ለልጆች ብዙም አያስቸግርም የሚል አደገኛ የተሳሳተ አረዳድ አለ። ይሁን እንጂ፣ ህጻናት በCOVID-19 እየታመሙ ከመሆኑም ባለፈ –አንዳንዶቹ በከባድ ታመው ለሆስፒታል እንክብካቤ እስከመግባት እየደረሱ በመሆኑ –መከላከያ ያስፈልጋቸዋል። መጠነኛ የCOVID-19 ህመም ያለባቸው ልጆችም ቢሆኑ

© Children's Hospital Colorado 2022 All rights reserved. Children's Hospital Colorado complies with applicable Federal civil rights laws and does not discriminate on the basis of race, color, national origin, age, disability, or sex. • ATENCIÓN: si habla español, tiene a su disposición servicios gratuitos de asistencia lingüística. Llame al 1-720-777-1234. • CHÚ Ý: Nếu bạn nói Tiếng Việt, có các dịch vụ hỗ trợ ngôn ngữ miễn phí dành cho bạn. Gọi số 1-720-777-1234. POP-611791P-2021-12

Children's Hospital Colorado

ከትምህርት-ቤት ሊቀሩ፡ ቶሎ ላይሻላቸው (ረጅም ጊዜ የሚቆይ COVID) እንዲሁም ከስንት አንዴም ቢሆን ልብን ሊጎዳ ለሚችል ከባድ ብግነት (መልቲሲስተም ኢንፍሌማተሪ ሲንድረም፣ ወይም MIS-C) ሊጋለጡ ይችላሉ። የCOVID-19 ክትባትን መውሰድ በሁሉም የእድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎችን በከባድ እንዳይታመሙ ወይም ለረጅም ጊዜ የቫይረሱ ጉዳት ሰለባ ሆነው እንዳይቆዩ የሚከላከሉበት የተሻለ መንገድ ነው።

ልጅዎን ብቁ እንደሆነ በፍጥነት ክትባቱን እንዲወስድ ማድረግ:

- በCOVID-19 የመያዝ የመያዝ ስጋቱን ይቀንስለታል።
- በCOVID-19 ከተያዘ ደግሞ በከባድ ከመታከም ይከላከለዋል።
- በቫይረሱ የመታመም እና የመሞት ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው የቤተሰብ አባላትን አባላትን ጨምሮ COVID-19ን ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳያስተላልፉ ያስችላቸዋል።

CDCን፣ የአሜሪካ ሕጻናት ሕክምና አካዳሚ እና የኮሎራዶ ህጻናት ሆስፒታልን ጨምሮ የሕክምና እና ሕብረተሰብ ጤና ባለሙያዎች፡ ሁሉም ብቁ የሆኑ ህጻናት እና ወጣቶች እራሳቸውን በቫይረሱ ከመያዝ እና ቫይረሱን ከማሰራጨት እንዲከላከሉ የCOVID-19 ክትባት መውሰድ እንዳለባቸው ይመክራሉ።

## የጎንዮሽ ውጤቶች ሊያሳስቡኝ ይገባል?

ክትባቱ ከባድ የጎንዮሽ ጉዳት አያስከትልም። ከክትባቶቹ አንዳንድ የጎንዮሽ ውጤቶች እንደሚከተሉ የሚጠበቅ ቢሆንም እንዲህ መሆኑ ግን የሰውነት በሽታ የመከላከል ስርአት እየሰራ ነው ማለት ነው። ህጻናት ላይ የሚታዩት የጎንዮሽ ውጤቶች አዋቂዎች ላይ ከሚታዩት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ የሚጠበቁ የCOVID-19 ክትባቶች የጎንዮሽ ውጤቶች መርፌ ከተወጋበት ቦታ ጋር የሚዛመዱ ሲሆኑ እንደ እመም፡ መቅላት እና እብጠት የመሳሰሉ ናቸው። አልፎአልፎ የሚታዩ የጎንዮሽ ውጤቶች ደግሞ ትኩሳት፡ ድካም ወይም የእጢዎች እብጠት ናቸው። እነዚህ ከብዙ ቀናቶች በኋላ በራሳቸው ጊዜ የሚጠፉ ሲሆን አደገኞችም አይደሉም። አብዛኞቹ ሁለቱንም ዶዞች የወሰዱ ሰዎች ከሁለተኛው ዶዝ በኋላ ኃይለኛ የጎንዮሽ ውጤት እንዳጋጠማቸው ሪፖርት አድርገዋል። እባክዎ የጎንዮሽ ውጤቶችን በተመለከተ ጥያቄዎች ወይም ማወቅe የሚፈልጓቸው ጉዳዮች ካሉሉ ዶክተርዎን ያናግሩ።

እንደ አናፊላክሲስ (anaphylaxis) የመሳሰሉ ከባባድ የጎንዮሽ ውጤቶች ከስንት አንዴ ነው የሚያጋጥሙት። እርስዎ ወይም ልጅዎ የበለጠ ከባድ የጎንዮሽ ውጤቶች እያጋጠማችሁ መሆኑን ካመኑ፣ ከሕክምና አቅራቢዎ ምክር ይጠይቁ። እርስዎ ወይም ልጅዎ ህይወታቹን አደጋ ውስጥ የሚከት የጎንዮሽ ጉዳት ካጋጠማችሁ፣ በ 911 ይደውሉ ወይም በአቅራብያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ህክምና ክፍል ይሂዱ።

## ከክትባት በኋላ ይከሰታል የተባለው ሚዮካርዲቲስ ሊያሳስበኝ ይገባል?

እርስዎን እና ቤተሰብዎን ከCOVID-19 የሚከላከሉበት የተሻለው መንገድ ክትባቱን መውሰድ ነው። የCOVID-19 ክትባትን ተከትሎ ለማዮካርዲትስ ወይም ለፔሪካርዲትስ (የልብ ወይም በልብ ዙርያ ያለው ከረጢት ዕብጠት) የመጋለጥ ስጋት ከስንት አንዴ የምያጋጥም ነው። በርግጥ፡ የCOVID-19 ክትባትን ተከትሎ

Children's Hospital Colorado

© Children's Hospital Colorado 2022 All rights reserved. Children's Hospital Colorado complies with applicable Federal civil rights laws and does not discriminate on the basis of race, color, national origin, age, disability, or sex. • ATENCIÓN: si habla español, tiene a su disposición servicios gratuitos de asistencia lingüística. Llame al 1-720-777-1234. • CHÚ Ý: Nếu bạn nói Tiếng Việt, có các dịch vụ hỗ trợ ngôn ngữ miễn phí dành cho bạn. Gọi số 1-720-777-1234. POP-611791P-2021-12

ማዮካርዲቲስ ወይም ፔሪካርዲትስ የመከሰት ዕድል በCOVID-19 መያዝን ተከትሎ ሊከሰት ከሚችል ማዮካርዲቲስ ወይም ፔሪካርዲትስ ያነሰ ነው። ከክትባቱ በኋላ ለማዮካርዲቲስ የተጋለጡ ህጻናት ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ ቶሎ እና ሙሉ በሙሉ ማገገም ችለዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ የCOVID-19 ክትባትን መውሰድን ተከትሎ ከስንት አንዴ የምያጋጥሙ የጤና ችግሮች (complications) ሊኖሩ ይችላሉ። ምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለብዎ ማወቅ ማለት ማናቸውንም የጎንዮሽ ውጤቶች በፍጥነት መረዳት ይችላሉ ማለት ነው። የማዮካርዲቲስ እና ፔሪካርዲትስ ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- የደረት ህመም
- ትንፋሽ ማጠር
- የልብ ምት መጨመር: የልብ መርገብገብ ወይም ፈጣን የልብ ምት

የCOVID-19 ክትባትን ከወሰዱ ከአንድ ሳምንት በኋላ እነዚህ ምልክቶች በእርስዎ ወይም በልጅዎ ላይ የታዩ መስሎ ከተሰማዎት የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት ይኖርብዎታል።

## ልጅ የመውለድ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች የCOVID-19 ክትባት ቢወስዱ ችግር አለው?

አሁን ለማርገዝ በማቀድ ላይ ያሉ ወይም ደግሞ በቀጣይ ጊዜ ልጅ ለመውለድ ያሰቡ ሰዎች የCOVID-19 ክትባት መውሰድ ይችላሉ። የCOVID-19 ክትባትን ጨምሮ የትኛውም አይነት ክትባት ከወሊድ ወይም ከማርገዝ እቅድ ጋር በተያያዘ ችግር እንደሚያስከትል የሚያሳይ ማስረጃ በአሁኑ ጊዜ የለም።

## ነፍሰ ጡር ሴቶች የCOVID-19 ክትባትን መውሰድ ይኖርባቸዋል?

ነፍሰ ጡር ሴቶች የሰውነታቸው የበሽታ መከላከል ስርአት የተዳከመ ስለሆነ የበለጠ በቀላሉ ሊታመሙ ይችላሉ። ይህ ማለት ነፍሰ ጡር ሴቶች ለከፋ የCOVID-19 ህመም የመጋለጥ ስጋታቸው ከፍተኛ ነው እንዲሁም በእርግዝና ወቅት በCOVID-19 የሚያዙ ከሆነ ለአሉታዊ የጎኒዮሽ ውጤቶች ሊጋለጡ ይችላሉ። በእርግዝና ጊዜ የCOVID-19 ክትባት መውሰድ በCOVID-19 በከባድ ከመታመም ሊከላከልልዎ ይችላል።

የአሜሪካ የማዋለድ ሕክምና እና የማህጸን ሕክምና አካዳሚ እንዲሁም CDC ነፍሰ ጡር ታካሚዎች የCOVID-19 ክትባት እንዲወስዱ በጥብቅ ይመክራሉ። ነፍሰ ጡር ከሆኑ እና ስለ COVID-19 ክትባቶች ጥያቄዎች ካሉዎት፣ የOBGYN ሙያተኛዎን ያነጋግሩ።

## ስለ COVID-19 ክትባቶች እና ስለ እርግዝና እንዲሁም ስለ ጡት ማጥባት ምን እናውቃለን?

የCOVID-19 ክትባቶች ደህንነትን በተመለከተ ለነፍሰ ጡር ሴቶች የሚሆን ዳታ እየጨመረ ነው ያለው። ለጊዜው የምናውቀው ይህን ነው:

© Children's Hospital Colorado 2022 All rights reserved. Children's Hospital Colorado complies with applicable Federal civil rights laws and does not discriminate on the basis of race, color, national origin, age, disability, or sex. • ATENCIÓN: si habla español, tiene a su disposición servicios gratuitos de asistencia lingüística. Llame al 1-720-777-1234. • CHÚ Ý: Nếu bạn nói Tiếng Việt, có các dịch vụ hỗ trợ ngôn ngữ miễn phí dành cho bạn. Gọi số 1-720-777-1234. POP-611791P-2021-12

Children's Hospital Colorado

- ነፍሰ ጡር እና በቅርቡ የፀነሱ ሴቶች ነፍሰ ጠጡር ካልሆኑ ሴቶች ጋር ሲነጻጸር ለከፋ የCOVID-19 ህመም የመጋለጥ ስጋታቸው ከፍ ያለ ነው።

- አነስተኛ የጽንስ መጨናገፍ ስጋት በተከተቡም ባልተከተቡም ሴቶች ላይ እኩል ነው።

- ነፍሰ ጡር ሆነው ክትባቱን የወሰዱ ሴቶች ራሳቸውን እና ጽንሳቸውን ከCOVID-19 መከላከል መቻላቸውን የቅርብ ጊዜ መረጃ ያሳያል። (COVIDን የሚዋጉ አንቲቦዲዎች የእትብት ደም ላይ ተገኝተዋል።)

- mRNA የተባለው የCOVID-19 ክትባት (Pfizer ወይም Moderna) የወሰዱ አጥቢ እናቶች ጨቅላ ህጻናቸውን ሊጠብቁ የሚችሉ አንቲቦዲዎች የጡት ወተታቸው ላይ መገኘታቸው ጥናቶች አሳይተዋል። እንዚህ በጡት ወተት ውስጥ የተገኙት አንቲቦዲዎች የመከላከል ደረጃቸው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ተጨማሪ ምርምር ያስፈልጋል።

- ጠንካራዎቹ የሃገራችን የክትባት አስተማማኝነት ቁጥጥር ስርአቶች የCOVID-19 የወሰዱ ነፍሰ ጡር ሴቶች ወይም ጨቅላ ህጻናቶቻቸው ጋር በተያያዘ ሊነሱ የሚችሉ የአስተማማኝነት ችግሮችን ገና ለይተው ማወቅ አልቻሉም።

እስካሁን የተገኙት ሳይንሳዊ ማስረጃዎች የሚያሳዩት በእርግዝና ጊዜ የCOVID-19 ክትባት መውሰድ ጥቅም ካለመከተብ ስጋቶች አንጻር ሲታይ የጎላ ጥቅም እንዳለው ነው። ለዚህም ነው የአሜሪካ የማዋለድ ሕክምና እና የማህጸን ሕክምና ኮሌጅ እና CDC ነፍሰ ጡር ወይም ጡት አጥቢ ሴቶች የCOVID-19 ክትባት እንዲወስዱ የሚመከሩት።

**ክትባቱን ከየት ማግኘት እችላለሁ?**

እንደ CVS፣ Walgreens፣ King Soopers፣ Safeway እንዲሁም Walmart የመሳሰሉ የገበያ ማእከላትን ጨምሮ የCOVID-19 ክትባት የሚያቀርቡ ብዙ ቦታዎች በአቅራብያዎ ይገኛሉ። ክትባቱ በነጻ የሚሰጥ ሲሆን መታወቂያ መያዝም አይጠበቅብዎትም። በአቅራቢያዎ ክትባት የሚሰጥባቸው ቦታዎችን ለማግኘት https://covid19.colorado.gov/vaccine ወይም https://vaccines.gov ን ይጎብኙ።

ኢንተርኔት የማግኘት ዕድል ከሌሉዎት፡ እገዛ ለማግኘት ወደ ዶክተርዎ ጽሕፈት-ቤት መደወል ይችላሉ፣ ወይም ዚፕ ኮድዎን ወደ 438-829 በጽሑፍ/በአጭር የጽሑፍ መልእክት መላክ ይችላሉ። በተጨማሪ በአቅራብያዎ ወደ ሚገኝ ፋርማሲ ወይም መድሀኒት ቤት በመደወል ቀጠሮ እንዴት መያዝ እንደሚችሉ መጠየቅ ይችላሉ።

ክትባት ወደ ሚወስዱበት ቦታ የሚያደርስዎት ማጓጓዣ ከፈለጉ፣ Mile High United Way's Ride United ፕሮግራም በመላ ኮሎራዶ ወደ ሚገኙ የክትባት ማእከላት ነጻ የማጓጓዣ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል (በእያንዳንዱ ቀን እስከ 25 ማይል)። ተጨማሪ ለማወቅ በ 2-1-1 ይደውሉ ወይም 211colorado.orgን ይጎብኙ።

© Children's Hospital Colorado 2022 All rights reserved. Children's Hospital Colorado complies with applicable Federal civil rights laws and does not discriminate on the basis of race, color, national origin, age, disability, or sex. • ATENCIÓN: si habla español, tiene a su disposición servicios gratuitos de asistencia lingüística. Llame al 1-720-777-1234. • CHÚ Ý: Nếu bạn nói Tiếng Việt, có các dịch vụ hỗ trợ ngôn ngữ miễn phí dành cho bạn. Gọi số 1-720-777-1234. POP-611791P-2021-12

Children's Hospital Colorado

እነዚህ በተደጋጋሚ ለሚቀርቡ ብዙ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጡ ከታማኝ ምንጮች የተገኙ ድረገጾች እና ቪድዮዎች ናቸው:

[የCOVID-19 ክትባት ማመንታት - Amharic on Vimeo]

የአለም ጤና ድርጅት: ክትባቶቹ የሚሰሩት እንዴት ነው?
https://www.who.int/news-room/feature-stories/detail/how-do-vaccines-work

January 2022

© Children's Hospital Colorado 2022 All rights reserved. Children's Hospital Colorado complies with applicable Federal civil rights laws and does not discriminate on the basis of race, color, national origin, age, disability, or sex. • ATENCIÓN: si habla español, tiene a su disposición servicios gratuitos de asistencia lingüística. Llame al 1-720-777-1234. • CHÚ Ý: Nếu bạn nói Tiếng Việt, có các dịch vụ hỗ trợ ngôn ngữ miễn phí dành cho bạn. Gọi số 1-720-777-1234. POP-611791P-2021-12

Children's Hospital Colorado